# አርትዮስ ትዮሎጂካል ኮሌጅ

አርትዮስ ትዮሎጂካል ኮሌጅ ከአለምገና ዞን ወንጌላዊያን አብያተ ክርስትያናት ህብረት ጋር በመተባበር "ፖለቲካና ክርስትና" በሚል ርዕስ ላይ ያዘጋጀው ሥልጠና

*ባይሣ ገመቹ ፈይሣ*

*ነሐሴ 16, 2012*

*አለምገና ሰበታ*

# ፖለቲካና ክርስትና

## መግቢያ

ክርስቲያኖች በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ አለባቸው ወይ የሚለው ጥያቄ ለዘመናት ውዝግቦችን ሲያስከትል የቆየ ጉዳይ ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን ልክ የካቶሊክና አንግሪካል ቤተክርስቲያናት እንዳደረጉት ሁሉ በፖለቲካው ውስጥ መግባት አስፈላጊ ነው በማላት አቋማቸውን ሲገልጹ የቀሩት ደግሞ የማርቲን ሉተርን ፈለግ በመከተል አማኞች በፖለቲካ ሜዳ ውስጥ ገብተው መገኜት የለባቸውም ነው በማለት ይሞግታል፡፡[1]

አንዳንድ ሚሲዮናዊ ተቋማት አንደ ሱዳን ኢንቴሪየር ሚሽን /Sudan Interior Mission (SIM)/ ያሉት ወደ አህጉራችን አፍሪካ መተው ወንጌልን በሚሰብኩበት ጊዜ የማርቲን ሉተርን ፍልስፍና በመከተል ክርስቲያኖች በፖለቲካው ውስጥ መሳተፍ የለባቸውም የሚል አቋም ሲያራምዱ እንደ ነበር ታሪክ ያወሳል፡፡ ከዚህም የተነሳ በእነዚህ ሚሲዮናዊያን የተተከሉት ቤተክርስቲናት ተመሳሳይ አቋም ይዘው ሲጓዙ ታይተዋል፡፡

ይሁን እንጂ ካላፈው ምዕተ አመት ሁለተኛው አጋማሽ ወዲህ ነገሮች እየተቀየሩ መተዋል፡፡ ቀድሞው የምዕራብ አፍሪካ የወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲት ፕሬዝዳንት የሆኑት ፕሮፌሰር ኮርናልዮስ አሉዋላ “በመንግስታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት መሳተፍ ከአማኞች የሚጠበቅ ትልቅ ኃለፊነት ነው” በማለት ክርስቴኖች በፖለቲካው ውስጥ ድርሻ እንዳላቸው አመላክተዋል፡፡ በተለይ በአህጉራችን አፍሪካ አብያተ ክርስትያናትና ክርስትያናዊ የሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚሽኔሪዎችን ሃሳብ ወደ ጎን በመተው ለምን በፖለቲካው ውስጥ ለመሳተፍ ፈለጉ ካልን ከዚህ በታች ያሉትን ሃሳቦች እንደ ዋና ምክንቶች ሲቀርቡ እናያለን፡፡

i. ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት፡ እ.ኢ.አ በ1960ዎች ውስጥ ታዋቂ የሆኑ ሰዎች እንደ ክዋሜ ንኩሩማ፣ ጁልየስ ኔሬሬ፣ ጆሞ ኬንያታ ያሉት አገራቸው ከወደቀችበት የቅኝ ግዢ ስርአት ነጻ ለማውጣት በፖለቲካው ውስጥ መሳተፍ ተገቢ እንደሆነ በማመን በመንቀሳቀሳቸው አመርቂ ውጤት አግኝተውበታል፡፡[2]
ii. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት፡ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ትልቅ ስልጣን የያዘው አካል በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በመልካም ወይም በክፉ መንገድ የማስኬድ እድል አለው፡፡ ፍትሃዊነትንና እኩልነትን ለማምጣት አማኞች በዚህ ዘርፍ ውስጥ ቢገቡ መልካም ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ብዙ ክርስቲያኖች የፖለቲካውን ባህር በገፍ እየዋኙበት ይገኛል፡፡
iii. ኃይማኖታዊ መልክ ያላቸውን ችግሮች ለመቅረፍ፡ እ.ኢ.አ ከ1950ዎች በፊት ቤተክርስቲያን ፖለቲካን እንደ ጉድፍ ማጣያ ስፍራ በማየት ስትሸሽውና ስትጸየፈው ነበር፡፡ ነገር ግን ከክርስቲያናዊ በጎ አድራጎት ድርጅቶች መስፋፋት ጋር በተያያዘ፣ የክርስቲያን ተማሪዎች ሕብረት መቋቋምን ተከትሎ የአማኙ ማህበረሰብ አመለካከት እየተለወጠ መጣ፡፡ በተለይ ምሳ 28፡2 “አስተዋይና አዋቂ ሰው ግን ሥርዓትን ያሰፍናል” የተባውን ቃል በመያዝ የክርስቲያኖችን ተሳትፎ ማበረታታት ተጀመረ፡፡

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና የፖለቲካ ጉዳይ

አማኞች በዚህ ጉዳይ ላይ ሊኖራቸው የሚገባው ግንዛቤ አንድ ግለሰብ በተወሰነ ጥቅሶች ላይ ብቻ በመንጠልጠል በሚሰነዝረው አስተያየት ላይ ብቻ መሆን የለበትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን በሁለንተናዊ መልኩ በማየት፣ የቤተክርስቲያንን ታሪካዊ ዳራ በመዳሰስ፣ አማኞች ያለፉበትን ተግዳሮቶች ከግምት በማስገባት ልንረዳው ይገባል፡፡ ስለዚህ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

[1] Samuel Waje Kunhiyop, African Christian Ethics, 2008, Zondervan, Nairobi.pp 82
[2] Ibid pp 84

i. አስተምህሮተ እግዚአብሔር፡ እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡ በፈጠረበትም ጊዜ ሁሉንም ዉብ አድርጉ ሰራው (ዘፍ 1፡ 21)፡፡ የሚታዩት ቁሳዊ ነገሮች በሙሉ እርኩሳን ናቸው የማይታየው ነገር ደግሞ የተቀደሰ ነው የሚለውን የግሪኮችን ከንቱ ፍልስፍና ልናስወግድ ይገባናል፡፡

ii. አስተምህሮተ ሰብዕ፡ ሰው በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ክብሩ ፍጥረት ነው፡፡ ነገር ግን ተፈጥሮን ጨምሮ ሰዎች ሁሉ በኃጢአት ተበከሉ (ሮሜ 5፡12-21)፡፡ ኃጢአት ማህበራዊ መስተጋብሮችን በመበከል አስተዳደራዊ ጭቆናዎችና አመጻዎች እንዲበረከቱ ምክንያት ሆነ፡፡ በዚህም ምክንት ተሰብራ እያነከሰች ላለችው ምድር መራራትና አስፈላጊውን ጥጋና መስጠት ከአማኞች የሚጠበቅ አደራ ነው፡፡

iii. ትምህርተ ድነት፡ የሰይጣን አለማ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዳስማማ በማድረግ በግዛቱ ውስጥ እያነሳቀለው ማኖር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ዓላማ ግን ማዳንና መታደግ ነው፡፡ ይህንን ውጊያ ከመለኮታዊ እርጋታ ውጪ ማሻነፍ ፈጽሞ አንችልም፡፡

iv. ስለ እግዚአብሔር መንግስት ያለው አስተምህሮ፡ በክርስቶስ ኢየሱስ የቤዛነት ሥራ ከዘላለም ሞት የመትረፍ ዕድል ያገኘን ሰዎች ሁሉ የምድር ጨውና ብርሀናን በመሆን የእግዚአብሔርን መንግስት የመስበክ ኃላፊነት ተሰቶናል (ማቴ 5፡13-16)፡፡ እንደ ክርስቶስ አምባሰደሮች ባለንበት ሁሉ የእግዚአብሔርን ባህሪ ማንጸባረቅ አለብን፡፡

የፖለቲካዊ ተሳትፎን በተመለከተ ከአማኞች የሚነሱትን ጥያቄዎች ከላይ በተዘረዘሩት መስፈርቶች ላይ ቆመን መስጠት አለብን፡፡ ስለ ፖለቲካ የሚነገሩ ሁሉ እውነት ናቸው ማለት አንችልም፡፡ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ቆመን ትክክለኛውን አቋም መያዝ ከምን ጊዜውም በላይ አስፈላጊ ነው፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፖለቲካ ምን ይላል

### ፖለቲካና  የብሉይ ኪዳን አስተምህሮ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ቤተክርስትያን በግልጽ ባትታይም እግዚአብሔር ግን ለራሱ የመረጣቸው ህዝቦች ነበሩት፡፡ እስራዔላዊያን ከግብጽ ሲወጡ ይመራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን ሰጣቸው፡፡ እሱ ከሞተ በኋላ ደግሞ ኢያሱን አስነሳላቸው፡፡ እርሱም ከሞተ በኃላ ለ300 አመታት ገደማ በመሳፍንት ያስተዳድራት ነበር፡፡ የመሳፍንት ዘመንም ካበቃ በኋላ በነገስታት ይተዳደሩ ነበር፡፡

እስራኤላዊያን በተለያዩ አስተዳደራዊ ስልቶች ውስጥ አልፈዋል፡፡ እነዚህ ስልቶች በሙሉ ስኬታማ ናቸው ባንልም ከእያንዳነዱ አስተዳደር ጀርባ ግን እግዚአብሔር ቆሞ ነገሮችን ሲቆጣጠር እንደ ነበር ግን በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡ በእነዚህም ጊዜያት ሁሉ የተሾሙት መሪዎች ለግላቸው ጥቅም ሳይሆን ሕዝቡን በፍትህና እኩልነት ያለ አድሎና መድሎ እንዲያገለግሉ ሲያዘቸው እናያለን፡፡ (ዘዳ 17፡16-17፣ መዝ 72፡1-4፣ ኤር 21፡12).

### ፖለቲካና  የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ

በአዲስ ኪዳን ዘመን ያለው የቤተክርስቲያንና የፖለቲካ ግንኙነት በብሉይ ኪዳን ዘመን ከነበረው የእግዚአብሔርና እስራኤላዊያን ግንኙነት በእጅጉ ይለያል፡፡ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የነበረው ጌታችን ኢየሱስ የፖለቲካ ጥያቄዎች ሲቀርቡለት ነበር፡፡ ለዚያም የተለያዩ ምላሾችን ሰቷአል፡፡ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የቶማስ አኪዩነስን ፍልስፍና በመከተል ቤተክርስቲያን በፖለቲካው ውስጥ ብትሳተፍ ምንም ችግር የለውም በማለት ከመንግስት ጋር ተጋብታ ትሰራ ነበረች አሁንም ቀጥላለች፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር በሙሉ መልካም ነው መንግስትና አስተዳደርም ከእነዚህ ፍጥረታት አንዱ ስለሆኑ ቤተክርስቲያን በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ብትሳተፍ የጽድቅን ተጽዕኖ ማማጣት ስለምትችል አማኞች በዚህ ጉዳይ ውስጥ መግባት አለባቸው የሚል አቋም ስታራምድ ቆይታለች፡፡

ከዚህ አቋም በተቃራኒ ፕሮቴስታንቶች የማርቲን ሉተርን አስተምህሮ በመከተል ሰው በኃጢአት ስለ ተበከለ ከእግዚአብሔር ተቃራኒ ሆን ይቆማል ብሎ ያስተማረውን ተቀብለው ነበር፡፡ ስለዚህ ሉተር በቤተክርስቲያንና በመንግስት ወይንም ፖለቲካ መካካል ትልቅ ልዩነት አለ በማለት ሲያስተምር ነበር፡፡ ይህም የተሳትፎ አይነትና ጥልቀት ብዙ ክርክሮችን ስላስከተለ በፕሮቴስታንቶች መካካል ብዙ ውዝግቦችናንና ልዩነቶች ፈጥሮ ሲንሚገት ዘሬ ደርሰናል፡፡.

## ቤተክርስቲያን በፖለቲካው ውስጥ መሳተፍ የለባትም የሚሉት ቡድኖች የሚያቀርቡት ምክንያቶች

አንዳንድ ምሁራን ቤተክርስቲያን በፖለቲካና መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ መሳታፍ የለባትም የሚለውን አቋማቸውን ሲያንጸባርቁ ከዚህ በታች ለውን እንደ ማስጃነት ያቀርባሉ፡፡

- ኢየሱስ ምድራዊና ሰማያዊውን መንግስት ለያይቶ አስቀምጧአል፡- እነዚህም ሁለቱ መንግስታት መኖራቸው ባይካድም ኢየሱስ ግን አማኞች በምድራዊ መንግስት ሥራ ላይ ማሳተፍ የለባቸው አላላም (ዮሐ 18: 36, ዮሐ 19:11)፡፡
- የአማኞች ትልቁ ኃላፊነት ወንጌልን መስበክ ነው፡- እንደዚህ ብለው የሚሚገቱ ሰዎች ማቴ 28፡19-20 ያለውን ክፍል ይጠቅሳሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ወንጌሉ በምድር ላይ በሁሉም ቦታዎች ላይ መሰበክ እንዳለበት ግን ይዘነጋሉ፡፡
- ክርስቲያናዊ የስነ ምግባር መርህ የተሰጠው ለአማኞች ብቻ ነው፡- አለማዊያን የክርስቲያኖችን የሥነ ምግባር መርሆችን ስለማይፈልጉ ተለያይተን መኖር አለብን ይላሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ሁሉ የሚፈልገውን ነገር በተለያዩ መንገዶች በግልጽ ቋንቋ አስቀምጧአል፡፡.
- ክርስቲያኖች የተቀደሱና ለእግዚአብሔር የተለዩ መሆን ይኖርባቸዋል፡- ብዙ አማኞች ፖለቲካ ቆሻሻ ውስጥ እንደ መዘፈቅ ስለሆነ በዚያ ውስጥ መግባት በጭራሽ የለብንም ይላሉ፡፡ ይህ በግማሽ እውነት ቢሆንም ብርሃንና ጨው መሆን ጨለማ ባላበት ስፍራ መሆኑን ይዘነጉታል፡፡
- ቤተክርስቲያን ተመሳሳይ ስህተት እንዳትሰራ፡- ቤተክርስቲያን ባለፉት ጊዜያት በተለይ የሮማን ካቶሊክና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከመንግስት ጋር በመመሳጠር ብዙ አጸያፊ ነገሮችን ሲሰሩ ነበር፡፡ ስለዚህ እኛው ከዚህ መማር ይኖርብናል፡፡ ይሁንና የአማኞች ተሳትፎ ተመሳሳይ ችግር ለመፍጠር ሳይሆን ለአለም ተስፋ ለመሆን እንዲሁም መንገድ ለማሳየት መሆን አለበት፡፡

በአጠቃላይ ቤተክርስቲያን በምድራዊ ጉዳይ ውስጥ ተጠላልፋ ተልኮዋን ገሸሽ እንዳታደርግ በፖለቲካው ወስጥ መሳተፍ የለባትም ይላሉ፡፡

## ቤተክርስቲያን በፖለቲካው ውስጥ መሳተፍ አለባት የሚሉት ቡድኖች የሚያቀርቡት ምክንያቶች

በሌላ ጎን ደግሞ ከሁለተኛው 20ኛ ምዕተ አመት ወዲህ የተወሰኑ ምሁራን ቤተክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ በመሳተፍ በጎ ተጽዕኖ ማማጣት እንዳለባት ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች በመያዝ ይሚገታሉ፡፡

- አማኞች በዚህ ምድር ላይ እስካሉ ድረስ ከፖለቲካ ውጪ መሆን አይችሉም፡፡ በቀጥታም ቢሆን በተዘዋዋሪ መንግስት የሚያስተላልፈው ውሳኔዎች የአገሪቱን ዜጎች የሚነካ ስለሆነ ከፖለቲካ ውጪ መሆን አይቻልም፡፡ ቤተክርስቲያን ወንጌል ለመስራት መሰረተ ልማቶች ያስፈልጓታል ደግሞም አያሌ ጉዳዮችን ለማስፈጸም ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር ትገናኛለች፡፡ ስለዚህ በፖለቲካ ውስጥ አልሳተፍም ብሎ መቀመጥ እንደ ሰባራ ዕቃ እራስን አስቦ ፋይዳ አልባ አድርጎ ተሸመድምዶ መኖር ተገቢ አይደለም ይላሉ፡፡
- እውነትን ተናግሮ ለፍትሕ ታግሎ ለማለፍ መሳተፍ ተገቢ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የእውነትን ፋና ይዛ፣ ለፍትህ ታግላ ብርሃን መሆን የሚያስከፍለውን የጽድቅ ዋጋ ከፍላ ለብዙዎች ተስፋ ሆና ለማለፍ በቆራጥነት መነሳት ግድ ይላታል፡፡

- ✞ እ.ኢ.አ በ1974 በአለም አቀፉ ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት ሕብረት በተፈረመው የሉሲያን ቃል ኪዳን (Lausanne Covenant) ውስጥም ሁሉም የቤተክርስቲያናት አማኞች በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ እንዳለባቸው ተስማምተው ተፋራርመዋል፡፡ በዚህም ቃልኪዳን ውስጥ በዋናነት ያተኮሩባቸው ነጥቦች ከዚህ በታች ተቀምጠዋል፡፡
  - ➢ ፍትህን ለማስፈን እግዚአብሔር በሚያደርገው ሥራ ውስጥ መሳተፍ ፣
  - ➢ እርቅን ለማድረግ እግዚአብሔር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ መገኘት፣
  - ➢ ሰላምን፣ ነጻነትን እኩልነትን ለማስፈን እግዚአብሔር በሚያደርገው ተጋባር ውስጥ የበኩላችንን መስራት፣
  - ➢ ሰውን በሰውነቱ እኩል ማክበርና መቀበል፤
  - ➢ የማንኛውንም ሰው ሙብት ከመጋፋት መቆጠብ፣
  - ➢ ሰውን ሁሉ ማገልገል፣
  - ➢ ማንኛዉንም አይነት ጭቆናና ከፋት መቃወም አለብን እና
  - ➢ የእግዚአብሔርን መንግስትና በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጠውን ጽድቅ ማሳየት፡፡

## <u>ተሳትፎአችን ምን መምሰል አለበት</u>

ቤተክርስቲያን በፖለቲካው ውስጥ በመሳተፍ ውጤት ማምጣት ትችላለች ብለን ከተስማማን ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች በሚገባ ማጤን ተገቢ ነው፡፡ በተለይ እ.ኢ.አ በ1937 በኦክስፎርድ በተደረገው ኮንፍራንስ ላይ ቤተክርስቲያን በፖለቲካው ውስጥ በምትሳተፍበት ጊዜ ከዚህ በታች የተቀመጡትን መርሆች ብትከተል መልካም ነው በማለት አስቀምጠዋል፡፡[3]

- ❖ በፖለቲካ ውስጥ በመሳተፍ ለውጥን ለማምጣት መስራት እንደ ቀላል ነገር መታየት ያለበት ነገር አይደለም፡፡ ይህንን ስታደርግ ግን ዋና ዓላማዋ የሆነውን ወንጌልን ወደ ጎን በመተው የመንግስትን ፖሊሲ ከግብ ለማድረስ መጣር የለባትም፡፡
- ❖ ቤተክርስቲያን ለሁሉ ነገር መፍትሄው እኔ ጋር ብቻ ነው ያለው በማለት በትዕቢት ውስጥ እንዳትወድቅ መጠበቅ አለባት፡፡ ፖለቲካ እራሱን የቻለ ሙ እንደ መሆኑ መጠን የራሱ አሰራር ያለው ነገር ነው፡፡ በፖለቲከው ውስጥ ላሉት አማኞች ተገቢ የሆነ ስልጠና በመስጠት መደገፍ እንጂ በሁሉ ነገር ውስጥ ካልገባሁ ማላት አደጋ አለው፡፡
- ❖ ክርስቲያኖች የፖለቲካ ፖርቲን በማቋቋም ከቤተክርስቲያን ጋር አጣምሮ ለማስኬድ ማሳብ ለከፉ ውድቀት ሊዳርግ ስለሚችል ከዚህ ድርጊት መቆጠብ ተገቢ ነው፡፡
- ❖ ቤተክርስቲያን ለመንግስት፣ ለመሪዎችና ለግለሰቦች መጸለይ አለባት፣
- ❖ በታማኝነትና በፍቅር መገዛት አለባት፣ መቃወም ያለባት ግን የመንገስት ትዕዛዝ የእግዚአብሔርን ቃል የሚጻረር ሲሆን በቻ ነው፡፡
- ❖ በበጎ አድራጎት፣ በልማት፣ እንዲሁም ፍትህን ለማምጣት መንግስት በሚሰራው ሥራ ላይ አብሮ መሆን አስፈላጊ ነው፡፡
- ❖ እውነትና ፍትህ ሲዛባ መሪዎችን በተገቢው መንገድ መተቸትና ተገቢ የሆነውን አሰራር መጠቆም፡፡
- ❖ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተሰራ በማንኛውም መንገድ የሚደርስበትን ጭቆና መቃወም አለባት፡፡
- ❖ በፖለቲከው ውስጥ የሚሳተፉትን አማኞችን በሥልጠና፣ በጸሎትና በምክር መደገፍ፡፡
- ❖ በመጨረሻም ቤተክርስቲያን ታማኝነቷ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ቃል ብቻ መሆን አለበት፡፡

ፖለቲከው የማህበረሰባችንን አኗኗር በተለያዩ መንገዶች ስለሚነካ እንደ ቀላል ነገር አይተን የምንተወው ጉዳይ አይደለም፡፡ በአህጉራችን እንዲሁም በሀገራችን ያለችው ቤተክርስቲያን በፖለቲካው መሳተፍ ተገቢ እንደሆነ የተስማሙ ይመስላል፡፡ ያልተስማሙበት ጉዳይ ቢኖር በምን ደረጃና ጥልቀት ነው በሚለው ዝርዝር ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ይህንን መወሰን ባንችልም በመጨረሻ ያሉትን ነጥቦች በሚገባ ከተገበርን ብዙ እንደሚጠቅመን ሙሉ ተስፋ አለኝ፡፡

---

[3] Ibid 101.

# አማኞች በአመጻና ጦርነት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው?

ባይሣ ገመቹ

## መግቢያ

የሰው ልጅ ታሪክ በአመጻና በጦርነት የተሞላ ነው፡፡ ይህም ጦርነት መነሻው ፖለቲካ፣ ማህበራዊ አልያም ኢኮኖሚያዊ መልክ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ በጊዜ ሂደት ውስጥ አማኞች በአመጻና ጦርነት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚለው ሃሳብ አሳሳቢ አጀንዳ እየሆነ ስለመጣ ምሁራንና የቤተክርስቲያን አባቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ምላሽ እየሰጡ መተዋል፡፡

አማኞች በአንድ ሀገር ወይንም በአንድ አከባቢ ለሚነሳው ብጥብጥ፣ ጥል፣ አልፎም ግጭትና ጦርነት ምን አይነት ምላሽ ሊኖራቸው ይገባል የሚለው የጽሁፌ ማጠንጠኛ ነው፡፡ ይህም ጥያቄ ምናልባት ችግር ቢከሰት ምን እናድርግ የሚለውን ለመገመት ሳይሆን ላለፉት ብዙ አመታት እየተከሰተ የነበረና ዛሬም ያለ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ በአገራችን እንዲሁም ደግሞ በክልላችንና በከተማዎቹ ወጣቶች ከፖለቲካ ጋር ተያይዞ ይታይ የነበረውን ችግር ለመፍታት ሰላማዊ ሰልፎችን ከማድረግ ጀምረው እስከ ኃይል እርምጃ ሲሄዱ ታይቷል አሁንም ደግሞ አለ፡፡ ይሁንና በቤተክርስቲያን ውስጥ በቂ የሆነ ትምህርት በዚህ ጉዳይ ላይ ስለማይሰጥ ወጣቶች ተቃውሞአቸውን እንዴት በተገቢና ውጤታማ መንገዶች መግለጽ እንዳለባቸው ያስተዋሉ አይመስልም፡፡

እኛው እንደ አንድ መንፈሳዊ ተቋምና የስነ መለኮት ትምህርት ቤት እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ችግሮች እንደሚመለከታቸው አገልጋዮች በዚህ ጉዳይ ላይ በአከባቢያችን ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ጋር መመካከር አስፈላጊ ነው ብለን በጽኑ እናምናለን፡፡ በዚህች ጽሑፍ ውስጥ በዋናነት ለጦርነትና ግጭት ምክንያት የሚሆኑ፣ በዚህ ላይ የተሰነዘሩ የተለያዩ አመለካከቶችን በመጨረሻም አማኞች ሊከተሏቸው የተገቡ የመፍትሄ መንገዶችን ለማየት እንሞክራን፡፡

## የጦርነትና ግጭት ምክንያቶች

በአፍሪካ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ከጥቃቅን ግጭቶች አንስቶ የብዙ ንጹሐን ሰዎችን እስከሚያጠፉ ጦርነት መከሰት ምክንያት የሆኑ ነገሮች ሰዎች ከሚደርስባቸው የተለያዩ ጭቆናዎች ለመትረፍ ሲሉ በሚያደርጉት መራራ ትግል እንደሆነ ሃግ ማክኩለም የተባሉት ሰው ይላገራሉ፡፡.[4] ፍትህ ሲጠፉ ማህበረሰቡ ከልክ ላለፈ ቁጣና ተስፋ መቁረጥ ይጋለጣሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የተነፈጉትን ፍትህ ለማምጣት በአመጻና ጦርነት ውስጥ መግባት ይጀምራሉ፡፡ በአህጉራችንና እንዲሁም በሀገራችን አመጻና ጦርነቶች እንዲቀሰቀሱ ምክንያት የሆኑት ነገሮችን እንደሚከተሉት ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

- ❖ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ፡- የአንድ አገር ምጣኔ ሀብት ማደግ ሲጀምር ዜጎች በዚያ ውስጥ በመሳተፍ ሕይወታቸውን ለማሻሻል መጣር ይጀምራሉ፡፡ ችግር መከሰት የሚጀምረው የተገኘው እኮኖሚና ዕድሎች በውስን ሰዎች ተይዞ የቀሩት የእነዚያ ሰዎች ተላላኪና ሰራተኞች መሆን ሲጀምሩ ነው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ በአብዛኛው የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝና የተገኘውን መልካም አጋጣሚ ሁሉ ለመቆጣጠር የሚደረግ አላስፈላጊ ፍልሚያ ለጦርነትና ግጭት ምክንያት ሲሆን ይታያል፡፡ ከዚህ ጫወታ ውጪ በመሆን የተጎዱት በመቀናጀት ጦርነትና አመጸ መቀስቀስ ይጀምራሉ፡፡
- ❖ ፖለቲካዊ ለውጥ፡ ብዙ ጊዜ በአፍሪካ ባለሥልጣን የሆኑት ደጋፊዎቻቸውን፣ አልያም ዘመዶቻቸውን በመሰብሰብ የዝርፍያ ዕድል ያመቻችላቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ክፍፍልና ቅራኔን ስለሚፈጥር የተቀሩት ሕዝቦች ፍትህን ለመፈለግ ተደራጅተው ለበቀል ይነሳሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ከቀላል ግጭት እስከ ከፍተኛ ጦርት የሚደርስ ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡
- ❖ ፍትሕና እኩልነት ሲጠፉ፡ የሰው ልጆች በአገራቸው ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን መሰረታዊ መብቶች ሲነፈጉ፣ እኩልነት ሲጠፉ፣ የመኖር መብታቸውን ማለትም ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን ያለ አግባብ ሲነፈጉ ወደ ግጭትና ጦርነት ሊያመሩ ይችላሉ፡፡

[4] Hugh McCullum :*The Angel have Left Us*: the Rwanda Tragedy and the Church (Geneva Word Council of Churches, 1995) Pp 78

አንድ ማህበረሰብ ፍትሕ ሲያጣ ምለሹ ምን መሆን አለበት ለሚለው ጥያቄ ሁለት ታላላቅ አማራጮች ይቀርባሉ፡፡ አንዳንዶች አመጻን በማስነሳት ለመብታችን መሟገት አለብን ይላሉ፡፡ የቀሩት ግን አመጻና ጦርት አውዳሚና አክሳሪ ስለሆነ በሰላማዊ መንገድ መታገል አለብን ይላሉ፡፡ እነዚህ ሁለቱን ተቃርኖዎች እንደሚከተሉት ለማብራራት እንሞክራለን፡፡

## አመጻ አስፈላጊ ነው የሚል አመለካከት

በማህበረሰቡ ውስጥ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የሚነሱት ፍትህ አልባነት ለመቅረፍ አመጻን አንደ ዋነኛ አማራጭ መጠቀም አለብን የሚሉት ቡድኖች ከዚህ በታች ያሉትን የመከራከሪያ ነጥቦች ያቀርባሉ፡

- ✓ አመጻ አንድ የተበደለ ሰው ለተነፈገው ፍትሕ የሚሰጠው ተፈጥሮአዊ ምላሽ ነው፡፡ ጠላቶቻችን ሲበድሉን ግፍና በደል ሲያደርሱብን ያንን ለመከላከል ተመጣጣኝ ምለሽ መውሰድ ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ መንግስት በስልጣን ላይ ለመቆየት ሕዝብን መጨቆን እንደ አማራጭ ከተጠቀመ እኛም ያንን መንግስት ለማውረድ መከተል ያለብን መርህ አመጻ ነው ይላሉ፡፡
- ✓ አመጻ የተፈለገውን ውጤት ቶሎ ያመጣል፡፡ ጨቋኝና አምባገነን መንግስት ፈንቅሎ ፍትህን ለማስፈን ከጥቃቅን ተቃውሞዎች ጀምሮ እስከ ከባድ ጦርነት ድረስ መተግበር አፋጣኝ እፎይታን ይሰጣል ይላሉ፡፡ ለዚህም በዚህ አይነት ሁኔታ ከሥልጣን የተወገዱትን አምባገነናዊ ነገስታት እንደ ሳዳም ሁሴን፣ ሞሃመድ ጋዳፊን እንደ ምሳሌ ያነሳሉ፡፡
- ✓ አመጻ ከምንም በላይ ተሰሚነት አለው፡፡ መንግስት ሰላማዊ ድምጽ፣ የፍትህ ውትወታዎችን ችላ ካለ አመጻ ትልቅ ድምጽ ስላለው ላይሰማ አይችልም፡፡ አምባገነናዊ መንግስታት የሚሰሙት ብቸኛው ድምጽ አመጻና ጦርነትን ብቻ ነው፡፡
- ✓ ሰላማዊ ድርድሮችና ውይይቶች ውጤታማ መሆን ሲሳናቸው ቀሪው አማራጭ አመጻ ብቻ ነው ብለው ይሞግታሉ፡፡ እንደ እነዚህ ሰዎች አመለካከት ባለሥልጣናት በትዕቢት ተሞልተው የደሃውን እንባ ማየት ሲሳናቸው ያለው ብቸኛው አማራጭ አመጻ ነው ይላሉ፡፡

ለውጥን ለማምጣት ካስፈለገ ፍትሃዊ ጦርነት መከተል አለብን የሚል ፍልስፍና መነሻው ፕሌቶና ሲሴሮ ሲሆኑ በቤተክርስቲያን ውስጥም በእነ አውግስቲንና አኩውነስ ተቀባይነትን በማግኘት አምባገነናዊ መንግስትን ለማስወገድ አመጻና ጦርነትን መከተል ተገቢ ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡

## አመጻ አስፈላጊ አይደለም የሚል አመለካከት

አመጻን መጠቀም ውጤታማ ያደርጋል የሚሉ ሰዎች አመለካከታቸውን ለመደገፍ ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ቢያስቀምጡም ከዚህ ተቃራኒ በመቆም የአመጻን አውዳሚነት በማንሳት ሰላማዊ መንገድ ብቻ ያዋጣል የሚሉ ሰዎች ሃሳባቸውን እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡

- ✓ የአመጻ ውጤት ሌላ አመጻ እንጂ ሰላም አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር አመጻ አመጻን ከማስፋፋት ባለፈ የሰላም መንገድ ሊሆን አይችልም፡፡ ዊንክ የተባለ ሰው “አመጻን በአመጻ ለመመከት ካሳብን እራሳችን የምንጠላውን ነገር ስናደርግ እናገኛለን ማለት ነው” ይላል፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ ደግሞ “ጥላቻን በጥላቻ ለመመከት መሞከር ጥላቻን ያበዛል የከዋክብትን ብርሃን በጋረዳው ድቅድቅ ጭላማ ላይ ሌላ አስፈሪ ጭለማ መጨመር ነው፡፡ ጨለማን በጨለማ ማስወደግ አይቻልም ይህን የሚያደርገው ብርሃን ነው፡፡ የጥላቻ የአመጻና የጦርነትን አዙሪት የሆነ ቦታ ላይ ካልሰበርነው አንድ ቀን ልንወጣ በማንችልበት አዘቅት ውስጥ ይጥለናል” ይላሉ፡፡
- ✓ አመጻ ለነፍስ መጥፋትና ለንብረት ውድመት ያጋልጣል፡፡ ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ መልክ ያላቸውን ግጭቶች ለመፍታት ጦርነትን እንደ አማራጭ መጠቀም በሰላማዊ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣል፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጦርነት ምን ይላል?

በማህበረሰባችን ውስጥ የተጓደለውን ፍትህ ለማምጣት እንዲሁም ፍትሃዊነትና እኩልነት እንዲኖር ለማድረግ እንደ ክርስቲያን አልፎም እንደ መሪና አገልጋይ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?መጽሐፍ ቅዱሳችንስ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላል? ምላሽ የሚፈልጉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በብሉይ ኪዳን በእስራኤላዊያን ዘንድ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል "ዓይን በዓይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር፣ ቃጠሎ በቃጠሎ፣ ቁስል በቁስል፣ ግርፋት በግርፋት ታስከፍላለህ" ዘፀ 21፡24-25 የሚል ሕግ ሰቶ ነበር፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ድንጋጌዎችን ሰጥቶ ነበር፡፡ ይሁንና እነዚህ ሕጎች በዚያው ዘመንና በብሉይ ኪዳን ዘመን ለሚኖሩ እስራኤላዊያን እንጂ በዚህ ዘመን ላለን አማኞች ሙሉ በሙሉ ተግባር ላይ እንደማይውል ጌታችን ኢየሱስ በትክክል አስረድቷል፡፡

አዲስ ኪዳን ውስጥ የተሰጡን ሕጎች ክፉውን በክፉ መመለስ እንደሌለብንና ከዚህ በተቃራኒው መልካም ማድረግ እንደሚገባን ነው የተጻፈው፡፡ በማቴ 5፡38-41 ውስጥ ጌታችን አዲስ ትዕዛዝ ሲሰጥ እናያለን "… እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉ አድራጊውን ሰው አትቃወሙት…. ወዳጅን ውደድ ጠላትህን ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ"፡፡ አለም ሁሉ በክፋት እንደ ተያዘ እናውቃለን፡፡ ለዚህ ችግር መፍትሄ ለመሆን ከፈለግን ጌታችን ኢየሱስ ባሰመረልን መንገድ ላይ መጓዝ አማራጭ ሳይሆን ከሞት ይልቅ ሕይወትን የመምረጥ ጉዳይ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ በዮሐ 18፡36 ላይ "የእኔ መንግስት ከዚህ ዓለም አይደለም ቢሆንማ ኖሮ አይሁድ እንዳይዙኝ ሎሌዎች ይዋጉልኝ ነበር" በማለት የመንግቱን ታላቅነትና ዘላለማዊነት ያሳያል፡፡ ይህን መንግስት በሰይፍና የምንጠብቀው በጦርነት የምናስፋፋው እንዳልሆነ ይነግረናል፡፡ እንዲሁም በማቴ 22:38-40 ላይ "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" በማለት አማኞች ፍትህን ለማምጣት ሊታጠቁት የሚገባ ከባድ መሳሪያ ፍቅርና እውነት መሆን እንዳለበት ያስተምራል፡፡

## አማኞች ሊከተሉአቸው የተገቡ መርሆች

በምንኖርበት ማሕበረሰብ ውስጥ ብርሃንና ጨው ሆነን ለመገለጥ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጓደለ የሄደውን ፍትህ ለመመለስ አማኞች ምን አይነት መርህ ቢከተሉ መልካም ነው ለሚለው ጥያቄ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ከዚህ በታች ያሉትን አማራጭ ሃሳቦች ያስቀምጣሉ፡፡

- እርቅና ተሃድሶን ለማምጣት በትጋት መስራት፡ ቤተክርስቲያን ለምትኖርበት ማሕበረሰብ የሰላምና የእርቅ አገልግሎት መስጠት ግዴታ አለባት፡፡ ከተጎዱት ጎን በመቆም መንከባከብ፣ ለተጨቆኑት ፍትህንና እውነትን ለማምጣት በሰላማዊ መንገድ መናገር ግድ ይላታል፡፡ ቤተክርስቲያን በአመጻ ሳይሆን ሰላማዊ በሆነ መንገድ የእርቅና የመቀራረብን ድልድይ ስትዘረጋ በሁሉም ሰዎች ዘንድ ተዓማኒነትና ተቀባይነትን እያገኘች ትመጣለች፡፡
- ፍትህን መጠበቅ፡ ቤተክርስቲያን ተግባር ባልታከለበት መንገድ እርቅ ይሻላል፣ ሰላም መውረድ አለበት፣ አመጻ መልካም አይደለም ማለቷ ተገቢ አይደለም፡፡ እውነትን በሰላማዊ መንገድ በመግለጽ ከተጉዱት ጎን በመቆም ፍትን ለማምጣት መታገል ካልቻለች አንዳች ተጨባጭ ውጤት ማምጣት አትችልም፡፡ የሚታይ ግልጽ በደል ሲኖር ከመናገርና ከመቃወም ይልቅ ዝምታን ከመረጠች ከግፈኞች በምንም መንገድ ልትለይ አትችልም፡፡ የሚታየውን ጦርንት አመጻ የማህረሰብን ችግር በግልጽ  በመቃወም ሳትወጣ ለይምሰል ብቻ ሰላም ይውረድ የምትል ከሆነ ከተጠያቂነት አታመልጥም፡፡
- ፍትህን በማምጣት ትግል ላይ፣ ጭቆናን የማጥፋት ሥራ ውስጥ፣ ሙስናን በመመከት ሂደት፣ የጥላቻን ባህሪይ በማረም ተጋድሎ ላይ፣ በዘረኝት ላይ ያነጣጠረን በደል በመመከት ተግባር ላይ በንቃት መሳተፍ አለባት፡፡ ፍትህን፣ እውንትን፣ እኩልነትን በህዝቦችና በህዝቦች መካካል ለማስፈን ቤተክርስቲያን ያለ አንዳች አድሎ እንደ እግዚአብሔር ቃል መስራት አለባት፡፡
- ቤተክርስቲያን ሁሉንም ሰዉ በእኩልንት የምትቀበል ሆና መገነት፡ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ያለ አንዳች አድሎና መድሎ በእኩልነት እግዚአብሔርን የሚያመልኩባት ሥፍራ መሆን አለባት፡፡ የአንድ ቤተክርስቲያን አባላት በሙሉ ዘር ላይ ያተኮረ መከፋፋል ሲመጣ ፍትህ ሲዛባ በአንድ ድምጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አቋምን ማንጸባረቅ አለባቸው፡፡
- በፖለቲካና መንግስታዊ አስተዳደር ላይ ሊኖረን የሚገቡ አቋሞችና አመለካከቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶች ሊገሩ ይገባል፡፡  ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫ ወስደውን ከሕይወት ጎዳና እንዳያስቱን ልጓም ሊበጅላቸው ይገባል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዮችን

በምንቃወምበትና በምንደግፍበት ጊዜ በጭፍን ጥላቻ አልያም ፍቅር በሌላ ጎን ደግሞ የግላችንን ወይም የብሔራችንን ጥቅም ብቻ እያሰላሰልን ከሆነ በእርግጥ ስተናል፡፡ ወገንተኝነታችን ቅድሚያ ለእግዚአብሔር ቃልና ለእውነት መሆን መቻል አለበት፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በአማሳሉ የተፈጠሩ ሰዎችን በመውደድ ለእርሱ ያለንን ፍርሃት ማሳየት ግድ ይላል፡፡ ታማኝነታችንና ወገንተኝነታችን ለእግዚአብሔርና ለቃሉ መሆን ነው ያለበት፡፡ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅርና አክብሮት በአማሳሉ የተፈጠሩ ሰዎችን በመውደድ መግለጽ አለብን፡፡

- ጠላቶቻንን ወድድ የበደሉንን ይቅር ማለት የእለት ተእለት ተግባራችን አድርገን መኖር አለብን፡፡ በእውነት ክርስቲያኖች ከሆንን ጌታችን በማቴ 5:44-45 ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብሎ ያዘንንን ትዕዛዝ ማክብር ግድ ይለናል፡፡ እንዲሁም የበደሉንን ይቅር ማለት የማንችል ከሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ እንደማናገኝ ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

አመጻ እና ጦርነት ጭቆናንና በደልን ለማስቀረት እንደ አይነተኛ መሳሪያ ተደርጎ በሥራ ላይ ሲውል የነበረ ነገር ነው፡፡ መንግስት አምባገነናዊ በመሆን ሕዝቡን ሲጨቁንና ሲበድል ብሶተኞቹ በመደራጀት ጦርነትን በማወጅ ያንን መንግስት ሲገለብጡ ኖረዋል፡፡ በዚህ መንገድ ሙኔድ አንዳች ውጤት የለውም ለማለት ባንችል እንኳ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ሲያመዝን ይታያል፡፡እንደ ክርስቲያኖች ስንመዝን ደግሞ በአመጻና ጦርነት መንገድ ላይ መገኘት ትልቅ አደጋና ኪሳራ አለው፡፡

ፍትሕና እኩልነትን ለማስፈን በሰላማዊ መንገድ መታገል አትራፊና ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ማገናዘብ ይቻላል፡፡ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ኒልሰን ማንዴላና ስትብ ቢኮ በሰላማዊ መንገድ ታግለው የነጮችን የበላይነት ለመቀልበስ ችለዋል፡፡ በአሜሪካ ውስጥም ማርቲን ሉተር ኪንግ በዘር ላይ የተመሰረተን መድሎና ጥላቻ በሰላማዊ መንገድ በመታገል ትልቅ ውጤት እንዳመጣ ከታሪክ መማር ይቻላል፡፡

በተለያየ መንገድ በሰው ልጆች ላይ ጉዳት የሚያመጡትን ጨቋኝ ስርኣቶችን በሰላማዊ መንገድ በመቃወም እነርሱን ወደ እውነት አምጥተን ሌሎችንም ከብዙ ውድምትን ኪሳራ መታደግ እንችላለን፡፡ ፍትህ አልባ የሆነውን መዋቅር እንዲሁም በተለያ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የተዘረጋውን ብልሹ አካሄድ በሰላማዊ መንገድ በመታገል ለሁሉም ጠቃሚ የሆነውን የሰላም ፍሬ ማግኘት ይቻላል፡፡